# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

**ቁጥር** 66 ነሐሴ 14 **ቀን** 2001 **ዓ.ም**

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

> ሌሎች በገነቡት ዲሞክራሲ ጥላ ስር ተጠልለንና ሌሎች በተሰዉለት ነፃነት እየኮራን ለግዜያዊ የግል ደህንነታችን ስንል ያንን ያስተማረንን ህዝብ ነፃነት እርግፍ አድርገን የረሳን ሰዎች ካለን እኛ ደህንነትም ነፃነትም በፍፁም አያስፈልገንም።
>
> አቶ **ኤፍሬም ማደቦ** ዴንቨር በግንቦት7 ስብሰባ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ

## ወያኔ ለውጭ ከበርቴዎች እየሸጠ ያለውን የህጋራችን ለም መሬት አስመልክቶ ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ

ነሐሴ 11 2001

ኢትዮጵያዊው ገበሬ መድፍና አዳፍኔ ይዞ የመጣን ወራሪ በጦርና በጋሻ መክቶ ያቆየውን መሬት ዛሬ "ኢንቨስተር" ተሰኝተው ሽር ጉድ በሚባልላቸው ከበርቴዎች እየተወሰደበት ነው። ድሮ ባንዳዎች ጠላትን መንገድ እየመሩ እንዳመጡ ሁሉ ዛሬም የወያኔ ሹሞች እነኚህን ዘመናዊዎቹን ወራሪዎች እገበሬው ማሳ ድረስ አምጥተው "ይኸ ይሻልዎታል ወይስ ያ" በማማረጥ ላይ ናቸው።

ወያኔ የኢትዮጵያን ለም መሬቶች ለባእዳን ለመሸጥ እንዲህ የተስገበገበው ለምድነው? ይህ ክስተት ስለወያኔ ባህርይ ምን ይነግረናል? ምን እርምጃስ ሊወሰድ ይገባል? የሚሉና የመሳሰሉ ጥያቄዎች በኢትዮጵያዊያን አእምሮ እተመላለሱ ናቸው።

በአሁኑ ሰዓት ወያኔ ሲያጭበረብርባቸው የነበሩት ጭምብሎች ሁሉ ተገፈዋል። የፈጣን እድገትና ‹‹ልማታዊ መንግሥትነቱ›› ውትውታ የአድማጭኝ ጆሮ አሰልችቷል፤ ከእንግዲህ ሰሚ የለም። እራሱ ባስለመደው ዘረፋ ሌላውም እየተበረታታ ወርቁ በባሌስትራ፤ ‹‹ኢንቬስትመንት›› በአጥር እየተተካ ሥርዓቱ ራሱ ያመጣው ቅጥ ያጣ ብልግና ሰለባ እየሆነ ነው። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለማፈን ያወጣው አዋጅ የእርዳታ ጅረት ሙሉ በሙሉ ወደራሱ ብቻ እንዲፈስ ማድረግ ያስቻለው ቢሆንም የጅረቱ የፍሳሽ መጠን እንዲቀንስ በማድረጉ ያልጠበቀው ውጤት አምጥቷል። እድገት አመጣሁ ሲል ረሃብ፤ ብርሃን አመጣሁ ሲል ጭለማ፤ ትምህርት አስፋፋሁ ሲል ድንቁርና፤ ዘመናዊ የጤና አገልግሎት ዘረጋሁ ሲል በሽታ፤ ጎረቤት አገርን ወርሬ አሸነፍኩ ሲል አሳፋሪ ሽንፈት ባጠቃላይ ወያኔ የሚለውና እየሆነ ያለው ነገር ተቃራኒ እየሆኑ በመምጣታቸው ተስፋ ቆርጧል። ይኸ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ‹‹ባወጣው ያውጣው፤ አገሪቷን ካፈራረስኩ አይቀር ወደፊትም እንዳትጠገን አድርጌ ላፍርሳት›› ወደ የሚል ሰይጣናዊ ድምዳሜ አድርሶታል። የኢትዮጵያን ለም መሬቶች ለባእዳን በተለይም ደግሞ ለአረብ ከበርቴዎች መስጠት ከመሬት ይዞታ መፋለስም ባሻገር ዘርፈ-ብዙ የሆነ ለትውልድ የሚቆይ ችግርን በቀላሉ መትከል መሆኑን ወያኔ በመረዳቱ ይህንን የመጨረሻ እድሉን ለመጠቀም ታጥቆ ተነስቷል።

ባእዳኑ የሚያፍሱት ምርት ለአገራቸው የሚፈልጉት በመሆኑ ለኢትዮጵዊያን ቁርስና ምሳ የሚያደርገው አስተዋፅዖ አይኖርም። በእነዚህ ተለምነው በመጡ ከበርቴዎች ላይ ተገቢ የቴክኒክ ቁጥጥር ይደረጋል **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## እነ ልደቱና የወጣቶች ማህበር ልዩ የስለላ ተልእኮ መቀበላቸውን መረጃዎች አጋለጡ

በህዝባዊ ተቃውሞ እየተወጠረ የመጣው ፋሽስቱ የወያኔ አገዛዝ እራሱ ያደራጃቸውን የወጣቶች ፎረምና የልደቱ አያሌውን ኢዴአፓ በስለላ ስራ ላይ ማሰማራቱን አንድ ከደህንነት የተገኘ መረጃ አጋለጠ።

መረጃው እንዳመለከተው ባለፈው ቅዳሜ የወያኔ የደህንነት መስሪያቤት ከየወረዳው ለተውጣጡ የስለላ ሰዎች በምስጢር ያዘጋጀው ስብስባ በገነት ሆቴል አቅራቢያ በሚገኘው የቀበሌ 09 ጽ/ቤት ውስጥ መካሄዱ ታውቋል። የስብስባው አጀንዳዎች "በግንቦት ሰባት እና የአንድነት ፓርቲ ውስጥ ግንኙነት ስለመኖሩ መከታተል፤ የበርከት ስምኦን ምክትል የነበረውና የወያኔን አገዛዝ ዘረኝነት ተቃውሞ በቅርቡ ለሥራ በተላከበት የአሜሪካን አገር ጥገኝነት ከጠየቀው ኤርሚያስ ለገሰ ጋር የቅርብ ግኑኝነት የነበራቸው ሰዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ መከታተል፤ እና በልደቱ አያለው ከሚመራው ኢደአፓ ጋር ጸጥታን ለማስከበር በጋራ ለመስራት ስለደተደረሰበት ስምምነት" የሚመለከቱ እንደነበረ ተገልጾአል። በዚህ ስብሰባ ረጅም የውይይት ጊዜ የፈጀው **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## መለስ ባደገኛ የጤና መታወክ ውስጥ መገኘቱ ታወቀ፣ እስከዛሬም በውጭ አገር በመታከም ላይ ነው

ከግንቦት 7 የቤተመንግስትና የበረራ ክፍል ምረጃ ምንጮቻችን በደረሰን ጥቆማ መሰረት፣ ዘረኛው መለስ ዜናዊ በደረሰበት ድንገተኛና ከፈተኛ የጤና መታወክ ምክንያት አርብ ሌሊት በቻርተርድ አውሮፕላን ወደ ቤልጂዬም ብራሰልስ አምርቷል። እስከዛሬም አለመመለሱን ለማረጋገጥ ተችሏል።

ዘረኛው መለስ ዜናዊ በተለከፈበት የአእምሮ በሽታ በተደጋጋሚ ወደ ብራሰልስ ይመላለስ እንደነበር ያስታወሱት ምንጮቻችን፣ የአሁኑን ጉዞውን ለየት የሚያደርገው ግን የሰውየው የጤና ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ ነው።

ቁጥራቸው 10 ከሚደርሱ አጃቢዎች ጋር የተጓዘው አምባገነኑ መለስ ዜናዊ፣ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሊደረግብኝ ነበር የሚል ዜና ካሰራጨ በኋዋላ በከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ መግባቱ የአጀቡን ቁጥር ለማብዛት እንዳስገደደው ምንጮቻችን ዘግበዋል። በትንሹም በትልቁም መርበትበትና መበርገግ የሚቀናው ዘረኛው መለስ፣ የእንቅልፍ ማጣት ችግር እንዳለበትና ያሁኑ በሽታውም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሊሆን እንደሚችል ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል።

ባለፈው ሳምንት መጨረሻ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ስብሰባ እንደተደረገ ተደርጎ በወያኔ መገናኛ ብዙሃን የቀረበው ዘገባ ፈጽሞ ሀሰት ነበር ያሉት ምንጮቻችን፣ ይህ የተደረገው የመለስ ዜናዊ ጤና መታወክ ሊፈጥር ይችላል ተብሎ የሚጠበቀውን የደህንነት ስጋት ለመቀነስ እንደሆነ የቤተመንግሥት ምንጮቻችን ከላኩልን ዜና ለማወቅ ተችሏል ።

የመለስ ህመምም ሆነ ካገር መውጣት በከፍተኛ ሚስጥር የተያዘ ሲሆን፣ ምናልባት ሰውየው አንድ ነገር ቢሆን በሚል **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## የአንድነት ፓርቲ ስብሰባ በረብሻ ተቋረጠ። በስብሰባው ላይ የተገኙት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና ፕ/ር በየነ ጴጥሮስን ተደበደቡ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ እሁድ ነሀሴ 10 2001 በአዳማ ማዘጋጃ ቤት ጠርቶት የነበረው ህዝባዊ ስብሰባ፣ ወያኔ ሆን ብሎ የተቋዋሚ መሪዎችን ለመዝለፍና ለማዋረድ ካምፕ አስገብቶ ባሰለጠናቸው ዱርዬዎች መቋረጡ ታወቀ። በስብሰባው በክብር እንግድነት የተኙት የቀድሞ ፕረዝዳንት ነጋሶ ጊዳዳንና ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስን ጨምሮ ስብሰባውን ለመምራት በቦታው የተገኙ በርካታ የአንድነት አባላት ላይ ድብደባ ተፈጽሟል።

በተቃዋሚወች የሚደረጉ ህዝባዊ ስብሰባዎችን በከፍተኛ ጩህት ፡ ፉጨትና ረብሻ ስለማስቆም ፣ በቅርቡ ስልጠና ከወሰዱት የመንደር ጎረምሶች መካከል፣ የተወሰኑት የእሁዱን የአንድነት ስብሰባ ለማወክ ሳይሳተፉ እንዳልቀረ ተገልጿል። ስብሰባው ተጀምሮ የመግቢያ ንግግር ከተደረገ በሓላ "አካሄድ" በሚል ቁጣ የተቀላቀለበት ጥያቄ ከአንድ የወያኔ ካድሬ ከተንሰና ያንን ተከትሎ በተነሰው ረብሻ ስብሰባው መቋረጡ የተዘገበ ሲሆን፣ ተሰብሳቢ መስለው የተሰገሰጉት ወያኔ ያሰለጠናቸው ዱርዬዎች ከስብሰባው ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ጥያቄዎችን በቁጣና በጩሐት ካነሱ በኋላ ስብሰባው እንዲቋረጥ ተደርጓል።

በተቃዋሚወች በሚደረጉ ህዝባዊ ስብሰባወች ላይ ረብሻ ለማስነሳት በወያኔ ስልጠና የወሰዱት የመንደር ጎረምሶች በተለየ ሁኔታ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን "ለነፍጠኞች አሳልፈው የሰጡን" በሚል መደብደባቸውን አውራምባ ታይምስ የተባለው ጋዜጣ መዘገቡ ይታወሳል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## የኦሮሞ ግንባርን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ባለ አራት ክፍል የቴሊቪዥን ዘገባ በኬንያ መተላለፉ ወያኔንን አስቆጣ

በኬንያ ታዋቂ የሆነው ኔሽን ቴሌቪዥን የኦሮሞ ነጻ አውጭ ድርጅት የጦር ሜዳ ውሎ ታሪክን በአራት ተከታታይ ክፍል ለሕዝብ ይፋ በማድረጉ የወያኔ አምባገነኖችን እጅግ እንዳስቆጣ ለማወቅ ተችሏላ። እንደ ዜና ምንጮች ዘገባ የኔሽን ቴሌቭዥን የመጀመርያውን ክፍል እንዳቀረበ የወያኔ ቁንጮዎች በመደናገጥ ቀሪው ፕሮግራም እንዳይተላለፍ በኢትዮጵያ የኬንያን አምባሳደር የሆኑትን ፍራንክሊን ኢሲፒላ መጠየቃቸው ተዘግቧል። የኬንያ ውጭ ጉዳይ ሚንስትርም ከወያኔ ገዢዎች የቀረበለትን ልመና አዘል ማስጠንቀቂያ ተቀብሎ ለኔሽን ሚዲያ ግሩፕ ፕሮግራሙ እንዲቋረጥ መልእክት አስተላልፎ የነበረ የኔሽን ኩባንያ ጥያቄውን ውድቅ በማድረጉ ሙሉውን ፕሮግራ እንዳስተላለፈ ታውቋል። ነገር ግን ወያኔ ከረሱ ድንበር አልፎ ህዝብ የማወቅ መብትን ለማፈን አደርጎት የነበረው ሙከራ የወያኔን ማንነት እርቃና ያስቀረ ነው ሲሉ አስተያየት ሰጪዎች ተናግረዋል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ወያኔን ለማስወገድ እንጣደፍ፤ በገዛ አገራችን የባዕዳን ጭሰኖች የሚያደርገንን የወያኔን የመሬት ሽያጭ ሴራ እንበጣጥስ

መለስ ዜናዊ የአገራችንን መሬት የሚያሻሽጡ ደላሎችን በአረብና በሌሎች አገሮች ማሰማራቱና ለዚህም የማሻሻጥ ሥራ ከፍተኛ ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ እየከፈለ መሆኑን ከጥቂት ወራት በፊት የግንቦት7 ንቅናቄ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ዛሬ ይህ የድለላ ሥራ ተሳክቶ ባዕዳን ለም መሬት ለመቀራመት ወደ አገራችን ኢትዮጵያ እየነጎዱ ነው፡፡ የወያኔ ቁንጮ መለስ ዜናዊም ሶስት ሚሊዮን ሄክታር ስፋት ያለውን ለም የአገራችንን መሬት ለእነዚህ ባዕዳን በመቸብቸብ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ለመሰብሰብ መቋመጡን ባለፈው ሣምንት ለውጭ መገናኛ ብዙሃን በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ እጁን እያሻሸ በመፍለቅለቅ ጭምር ገልፆአል፡፡

ግንቦት7 ይህ የሃገራችንን መሬት ለባዕዳን የመሸጥ መርሃ-ግብር ወያኔ እስከዛሬ ካካሄዳቸው ፀረ-አገር እና ፀረ-ሕዝብ ድርጊቶች ሁሉ የከፋና አድማሱም የሰፋ ነው የሚል እምነት አለው፡፡ በተጨማሪም ወያኔ እስከዛሬ በሃገራችን ሃብት ላይ ካካሄዳቸው ዘረፋዎች በሙሉ የበለጠ፤ እጅግ ግዙፍ የሆነ የዘረፋ መስክ ነው ብለን እናምናለን፡፡

ድርጊቱ ፀረ-አገር ነው ያልነው ተከታታይ ትውልድ የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን፣ ምድሩን፣ አፈሩን ለመከላከል የከፈለውን መስዋዕትነት ግምት ውስጥ በማስገባት፤ አባቶቻችንና እናቶቻችን ልዩ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር የኢትዮጵያ መሬት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባዕዳን አይያዝም በማለት ለዘመናት ያጸኑትን አገራዊ ህግ የሚጥስ ስለሆነ ነው፡፡ ድርጊቱ ፀረ-አገር ነው ስንል ባዕዳን እንዲህ በስፋት የመሬት ባለቤቶች በሚሆኑበት አገር ኢትዮጵያዊውን ዜጋ ከሃገሩና ከመሬቱ ባለቤትነት ስሜት ነቅሎ ውርደቱ የማያበቃ የባዕዳን ጭሰኛ ያደርገዋል ማለታችን ነው፡፡ ፀረ-አገር ነው የምንለው መለስ ዜናዊ መሬት ተቀራመቱ ብሎ የፈቀደላቸው ለከባቢው አየር፤ እጅግ በጣም ስሱ ለሆነ የሰው የእፀዋትና የእንስሳት ሚዛናዊ ግንኙነት ደንታ የማይኖራቸው፤ የተቻላቸውን ያህል ከሃገራችን ምድር ለመዝረፍ የሚመጡ ባዕዳን ነጋዴዎች መሆናቸውን፤ ብዙ ለማምረትና ለማትረፍ ሲሉ መሬታችንን፣ ወንዞቻችንንና እፀዋቶቻችንን ለአንዴና ለሁሌ ማውድም የሚችሉ አደገኛ የማዳበሪያ ኬሚካሎች፣ የእህልና የሰብል ዘሮች ይዘው የሚመጡ እንደሆነ ስለምናውቅ ነው፡፡ ድርጊቱ ፀረ-አገር ነው የምንለው ወያኔ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያን ራሳችንን፣ ወገናችንና ሃገራችን ለመጥቀም በእርሻ ሥራ እንሰማራ በማለት ያቀረቡትን የመሬት ጥያቄ ባለማስተናገድ ተስፋ እንዲቆርጡ ካደረገ በኋላ ይህንኑ ሃገሬው ጠይቆ የተከለከለው መሬት ለባዕዳን አሳልፎ ለመቸብቸብ በሃገራችን ላይ የዘመናዊ ቅኝ ተገዥነትን ለመጫን ታቅዶ የሚፈጸም መርሃ-ግብር መሆኑን ስለምናውቅ ነው፡፡

ይህ ድርጊት ፀረ-ሕዝብ ነው የምንለውም በበርካታ ምክንያቶች ላይ ቆመን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ገበሬ ቁጥር በመጨመሩና የእርሻ መሬት ከትውልድ ትውልድ ደግሞ ደጋግሞ እየተከፋፈለ ዛሬ የአንድ ኢትዮጵያዊ አርሶ አደር ቤተሰብ አማካይ የነፍስ ወከፍ የመሬት ይዞታ ከግማሽ ሄክታር በታች ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በገጠር ከሚኖሩት ሃያ የገበሬ ቤተሰብ መሃል ሶስቱ ማለትም አስራ አምስት በመቶው ጭራሽ መሬት የላቸውም። በራሱ በወያኔ መረጃ መሠረት በመሬት እጦት ምክንያት 200 ሺህ ያህል ዜጎቻችን በከተሞች ውስጥ በልመና ተሰማርተዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከ10 እስከ 15 በመቶው በቋሚነት ከውጭ መንግሥታት ከሚገኝ የእህል እርዳታ ነፍሱን ከስጋው አጣብቆ የሚያድር ነው፡፡ በእንዲህ አይነቱ አስከፊና አሳዛኝ እውነታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተሰንጎ በተያዘበት ሁኔታ ነው ወያኔ የሃገራችንን ለም መሬት በሙሉ እህልና ጥራጥሬ እያመረቱ የአገራቸውን ህዝብ ለመቀለብ ቆርጠው ለተነሱ የመንግስታት ተወካዮችና ባዕዳን ነጋዴዎች ለመቸብችብ ቆርጦ የተነሳው፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ከዚህ በላይ ፀረ-ሕዝብ ድርጊት ለማሰብ ይቸግረዋል፡፡

ይህ የኢትዮጵያን ለም መሬት የመሸጥ የወያኔ ድርጊት የዘረፋዎች ሁሉ እናት ነው እንላለን፡፡ ቀደም ሲል የግንቦት7 ንቅናቄ እንደገለፀው መለስ ዜናዊ ባዕዳንን መሬት ግዙኝ ብሎ ከመጋበዙ በፊት ጥሩ ዋጋ ያወጣሉ በተባሉ ቦታዎች ሁሉ እጅግ ሰፋፊ የሆኑ ለም መሬቶችን ወያኔዎች ለራሳቸውና ቤተሰቦቻቸው በነፃ አከፋፍለዋል። እንደሚታወቀው ለነመለስ መሬት ለመውሰድ ምስለኔዎቻቸውን በስልክ ማዘዝ ይበቃቸዋል። ለምሳሌ የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን በቋራ ብቻ 40 ሽህ ሄክታር መሬት መውሰዷን ከዚህ በፊት መግለፃችን ይታወሳል፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም ስዩም መስፍን በልጁ ስም እንዲሁ በመቶ ሽዎች ሄክታር የሚቆጠር መሬት አፋር ክልል ውስጥ በመውሰድ ያለምንም ዋስትና ከመንግስት ባንክ በወሰደው 50 ሚሊዮን ብር አነስተኛ የይስሙላ ሥራ አስጀምሮ መሬቱ ለባዕዳን ሃብታሞች ለመሸጥ ገዥ እየተጠባበቀ ነው፡፡ ሌሎችም የወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣናት እንዲሁ የሰፋፊ የገጠር መሬት ጌቶች ናቸው፡፡ እነዚህ በ1966 የአብዮት ወቅት እነራስ መስፍንን የባብለዙ ጋሻ መሬት ጌቶች ናቸው በማለት ሲያወግዙ የነበሩ ግለሰቦች ዛሬ «ራስ» ተብለው አይጠሩ እንጂ በያዙት መሬት ስፋትማ ቢበልጡ እንጂ አያንሱም፡፡ ልዩነቱ የቀድሞ መሳፍንት የሚወቀሱበት ብዙ ነገር የነበራቸው ቢሆንም ከያዙት መሬት አንድ ሄክታር እንኳን ለባዕዳን አሳልፈው የማይሸጡ ብሄራዊ ክብርና ፍቅር የነበራቸው ነበሩ። በፀረ-ኢትዮጵያዊነት የሚነዱት የዘመናችን የወያኔ ጉልተኞች ግን በነፍጥ የወረሩትን ግዛት ለነጩ፣ ለቢጫውና ለአረቡ በሚሊዮኖችና በቢሊየኖች በሚቆጥር ብር ሸጠው ገንዘቡን በውጭ አገራት ባንኮች ለማስቀመጥ አሰፍስፈዋል።

የኢትዮጵያን ለም መሬት በተጠና መንገድ አስቀድመው ስለተቀራመቱት መሬት ለመግዛት ወደ አገራችን የሚመጡት ባዕዳን ግዢውን የሚፈጽሙት መለስ እንዳለው ከመንግሥት ሳይሆን ከራሳቸው ከወያኔ ባለሥልጣናትና ቤተሰቦቻቸው ሊሆን ነው። እዚህ ላይ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ልብ ሊለው የሚገባው ጉዳይ ቢኖር እነዚህ የወያኔ ዘረኛ ባላባቶች ለባዕዳኑ ከሚቸብችቡት መሬት መሃል አንድ ሄክታር እንኳን በትግራይ ክልል ውስጥ የማይገኝ መሆኑ ነው፡፡ ይህ የወያኔ የዘረፋ እቅድ እስከዛሬ ወያኔ እነ ኤፈርትን በመጠቀም ያካሄደውን ዘረፋ የልጆች ጨዋታ የሚያስመስል፤ መጠኑንና ስፋቱ ለማሰብ የሚቸግር ትልቅ - በጣም ትልቅ የዘረፋ እቅድ ነው፡፡ ይህ ዘረፋ በጣም በዝቅተኛ ስሌት በአጭር ግዜ ውስጥ ከ30 ቢሊዮን የአሜርካ ዶላር በላይ ወደ ወያኔ ኪስ የሚጨመር እንደሆነ ይገመታል፡፡

ወያኔ ይኸንን ፀረ-አገር እና ፀረ-ሕዝብ የሆነውን ከፍተኛ የዘረፋ መርሃ-ግብሩን በተግባር ለማዋል ቆርጦ ተነሰቷል፡፡ ከላይ እንደገለፅነው ይህ እኩይ መርሃ-ግብር የወያኔን ባለስልጣናትን በኢትዮጵያ ብር ሳይሆን በአሜሪካ ዶላር በአንድ ጀንበር ሚሊዮነሮች ለማድረግ ታቅዶ እየተፈፀመ ያለ ድርጊት ነው፡፡ በዚህም ላይ ይህን እኩይ መርሃ-ግብር ወያኔ የሚፈፅመው ህገ-ወጥ በመሆነ መንገድ የያዘውንና አገራችንን ለማጥፋትና ለመዝረፍ ያስቻለውን የስልጣን እድሜ የሚያራዝም የሃብት ክምችት ይሰጠኛል ብሎ በማሰቡ እንደሆነ ግንቦት7 ጥርጣሬ የለውም፡፡ ከዚህ የመሬት ሽያጭ ከሚገኝ ገንዘብ የተወሰነው ወያኔ ሕዝብን አፍኖ የሚገዛበትንና ገንዘብ ፈሶበትም ጠገብኩ የማይለውን የወታደራዊና የሰለላ ጭራቆቹን ለመመገብ የሚጠቀምበት እንደሚሆን ግልፅ ነው፡፡ የወያኔን መሰሪ ዓላማዎች በሚመለከት የዘረዘርናቸው ነጥቦች ለግንቦት 7ም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ግኝት አይደሉም፡፡ በዓይነቱ የተለየ፤ በግዝፈቱ የላቀ፤ በዘረኝነት የታጀበ ፀረ-አገርና ፀረ-ሕዝብ ዘረፋ ሲገጥመን ጥቂት ለማለት ስለምንገደድ ነው ይኸንን ጉዳይ ያነሳነው።

ዋነኛው ቁም ነገር «ወያኔ በአገራችንና በእያንዳንዳችን ሕይወትና እጣ ፈንታ ላይ ምን ዓይነት ወንጀልና ግፍ እየፈጸመ ነው?» የሚለው ሳይሆን «እኛ ይህንን ወንጀል በደልና ግፍ ለማስቆም ምን እየሰራን ነው?» የሚለው ነው፡፡

በዚህ የወያኔ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ሕዝብ ወንጀልና በደል ያልተነካ ዜጋ አለ ብለን አናምንም፡፡ ይህ ከሆነ በዚህ ድርጊት የማይቆጭ ኢትዮጵያዊ የሲቪልም ሆነ የፖለቲካ ድርጅት የለም ማለት ነው፡፡ በዚህ ድርጊት ያልተቆጨ መሣሪያ ያነሳ ነፃ-አውጪም ሆነ ያለመሳሪያ ሕዝቤን እታደጋለሁ የሚል ህጋዊና ሰላማዊ ታጋይም አይኖርም። በዚህ እኩይ ተግባር የማይነካ የዘውግ ኅብረተሰብ፣ የእምነት ተከታይ፣ የጾታና የእድሜ ቡድን አይኖርም፡፡ የወያኔ በደልና ግፍ ፅዋው ሞልቶ ፈሷል፡፡ ሁላችንንም አዳርሷል፤ ሁላችንም ነክቷል፡፡ በዚህ በደል ፊት የጋራ ቁጣችን በተግባር መግለጽ ፍቱን የበደሉና የግፉ ማርከሻ መሣሪያ መሆኑን ሁላችንም የተረዳን ይመስለናል። ምንም አይነት የግልና የድርጅት ሽንገላና ሸወዳ ይህንን ሃቅ መሸፈን ከማንችልበት ደረጃ ላይ አድርሶናል፡፡ ምርጫችን እያንዳንዳችን በመረጥነው የትግልና የፖለቲካ ስልት፤ በመረጥነው የአደረጃጀት አግባብ ተሰባስበን ወያኔን አምረን መታገል ነው፡፡

ግንቦት7 ወያኔ የሚፈጽመው ፀረ-አገር እና ፀረ-ሕዝብ ድርጊት እንዲሁም የተዘፈቀበት የጭፍጨፋና የሙስና ማጥ ይህ በድን ገና ከመነሻው ህሊና ያልዘራበት በመሆኑ የተከሰተ ነው የሚል እምነት አለው፡፡ ራሳችንንና ሃገራችን ለምንገኝበት አሳፋሪና አሳዛኝ ሁኔታ መፍትሄው ይህንን ህሊና የለሹን ብካይ አገዛዝ ማስወገድ ብቻ ነው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሁም ወያኔን በማናቸውም መንገድ ለሚቃወሙ ኃይሎች በሙሉ የምናደርገው ጥሪ «ወያኔን የመሰለ እኩይ ኃይል ታግሎ ከመጣል ውጭ ሌላ አማራጭ የለንም» የሚለውን የግንቦት7 ንቅናቄ ጥሪ ሃቀኛነት እንዲመረምሩና ለጥሪውም በሚመቻቸው ዘዴና መንገድ ምላሻቸውን በአፋጣኝ እንዲሰጡ ነው፡፡

ጥሪያችን በአገዛዞች መካነ መቃብር በወያኔ የመቃብር ድንጋይ ላይ «ሕዝብን ሲንቅና አገርን ሲያዋርድ የነበረው የኢትዮጵያ የመጨረሻው አምባገነን አገዛዝ - ወያኔ - እዚህ ወድቋል!!!» የሚል ተጽፎ ለማየት እንጣደፍ ነው፡፡ ይህን ማድረግ ተስኖን ለወያኔን እድሜ ከሰጠነው ግን በአገሮች መቃብር ቤት እጅግ አሳዛኝ የህልፈት ታሪክ የተፃፈበት ድንጋይ የውዷ እናታችን የኢትዮጵያን እንደሚሆን ለአንዲት ደቂቃም አንጠራጠር።

# ሃይለ ሀሳብ

## ኢትዮጵያ ዛሬም የብሔረሰቦች እስር ቤት ናት!

ግንቦት 7 በደንቨር በጠራው ስብሰባ ላይ **በኤፍሬም ማደቦ** የቀረበ **ክፍል 2**

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሲወለድ ነፃ ነዉ-- ከሌሎች ጋር እኩል ነዉ-- ክቡር ፍጥረት ነዉ--- ሙሉ መብት አለዉ።

እነዚህ ነገሮች አንድ ሰዉ ኢትዮጵያዊ ስለሆነ ሳይሆን ሰዉ የሆነ ፍጡር ሁሉ ሲወለድ አብረዉት የሚወለዱ የተፈጥሮ ስጦታዎች ናቸዉ።ሰዎችን በጎሳ፤በዘር በሐይማኖትና በቆዳ ቀለም እየለየን እነዚህን የተፈጥሮ ስጦታዎች ማገድ ወይም መከልከል የተፈጥሮን ህግ መዋጋት ነዉ። ዘረኝነት የተለያየ የእድገት ደረጃዎች አሉት፡ እጅግ የከፋዉና ጨካኝ የሆነዉ የዘረኝነት የእድገት ደረጃ ጀኖሳይድና አፓርታይድ ነዉ፤ ሌላዉ ደግሞ በሚታይና በማይታይ መልኩ ገገር መደቦች ከራሳቸዉ ጎሳ ዉጭ የሆኑትን ሌሎች ጎሳዎች ከፖለቲካዉ ስርአት አርቀዉ የሲቪል፤የማህበራዊና የኤኮኖሚ መብታተቸዉን ሲረግጡ ነዉ።ብዙ ግዜ ዘረኝነት ሲባል ማጆሪቲ ሁሌም ማይኖሪቲን የሚበድል ይመስለናል፤ በብዙ ቦታዎች እንዳየነዉ ግን ማይኖሪቲም ቢሆን የፖለቲካ ሥልጣን በብቸኝነት እጁ ዉስጥ ሲገባ የዘረኝነት ባሕሪዩን በማጆሪቲዉ ላይ ማሳየቱ አይቀርም። ለዚህ ደግሞ አገራችን ኢትዮጵያና የቀድሞዋ ደቡብ አፍሪካ አይነተኛ ምሳሌዎች ናቸዉ።

ዘረኝነት ማንም ሰዉ በፍፁም አይቶት ሊያልፈዉ የማይገባ ከምናዉቃቸዉ በሽታዎች ሁሉ እጅግ የከፋ በሽታ ነዉ። ዘረኛነት በደሉ በቀጥታ የሚደርስበትን ሰዉ ብቻ ሳይሆን በዳዩንና ሌሎችንም አጠገቡ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ የሚያሰቃይ ማህበራዊ ነቀርሳ ነዉ። ዘረኝነት ከተወገደ በኋላም ቢሆን ጥሎት የሚያልፈዉ ህምም በዳዩንም ሆነ ተበዳዩን ለብዙ ግዜ የሚያሰቃይ መጥፎ በሽታ ነዉ። ዛሬ ወያኔን ዘረኛ ነዉ እያልን የምናስተምረዉና የምናስጠነቅቀዉ የበደሉ ገፈት ቀማሽ የሆነዉን ብዙኋኑን የኢትዮጵያን ህዝብ ብቻ አይደለም። አድሎ በነገሰባትና የህግ የበላይነት በማይታወቅባት ኢትዮጵያ ዉስጥ ጥቅም ፍለጋ ወያኔ በገነባዉ የዘር መሰላል ወደ ላይ ወጥተዉ ሌሎችን ቁልቁል መመልከት የሚዳዳቸዉን ምሁራንና ሌሎችንም የህብረተሰብ ክፍሎች ጭምር ነዉ። ወያኔ ዘረኛ ነዉ ስንል ይህ አባባላችን ፍፁም ኢትዮጵያዊ የሆነዉን ኩሩዉን የትግራይ ህዝብ እንደማያጠቃልል ለደቂቃም ቢሆን ሊዘነጋ አይገባዉም።ወያኔ ግን ዘረኝነቱንና ማን ይነካኛል ባይ ጀብደኝነቱን ሲገልፅ - ወያኔ ምርጥ ዘር ነዉ - ወይም ወያኔ የበላይ ነዉ እያለ አይደለም - ለዚህ እርኩስ ተግባሩ የሚጠቀመዉ የትግራይን ህዝብ ነዉ፤ይህ ደግሞ ሁለት ከፍተኛ አደጋዎች አሉት፡ አንደኛ- ሌላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የትግራይን ህዝብ የጎሪጥ እንዲመለከት ያደርግና በህዝብ መካከል ጥላቻ ይፈጥራል። ሁለተኛ- ሌሎች ብሔረሰቦች የወያኔን ዘረኝነት ለመዋጋት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሌላ የዘረኝነት ስሜት ይፈጥርና ጭራሽ አገሪቱ በቀላሉ ወደማትወጣዉ የእርስ በርስ ጦርነት ዉስጥ ትገባለች።

እንግዲህ ዘረኝነትን በዚህ መልኩ ከተረዳን የወያኔ አገዛዝ ዘረኛ ነዉ ስንል ምን ማለታችን ነዉ? ቀለል ባለ አነጋገር ወያኔ የሰዎችን ማንነት የሚለካዉ ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዳሉት በእያንዳንዱ ሰዉ የባህሪይ ይዘት ሳይሆን የሰዎችን የዘር ሐረግ ጀርባ በመመርመር ነዉ። ሦስት ነገሮችን እንመልከት፡-

1. ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ የወያኔ አገዛዝ ሰዎችን በቡድ ካልሆነ በቀር በግል አያዉቃቸዉም - ምን ማለት ነዉ? ወያኔ ግለሰቦች በኢትዮጵያ የፖለቲካ፤ የማህበራዊና የአኮኖሚ ዘርፎች ዉስጥ የሚጫወቱትን ሚና የሚወስነዉ በግለሰቦቹ ባህሪይና ችሎታ ሳይሆን የዘር ሀረጋቸዉን እየቆጠረ ነዉ። በግለሰብ ደረጃ ለወያኔ የግለሰቦች ችሎታ፤ ልምድ፡ የትምህርት ደረጃና ፀባያቸዉ ዋጋ የለዉም። ለወያኔ ትልቁ ቁም ነገር ግለሰቦቹ የመጡበት ጎሳና ዘር ነዉ (ለዚህ ነዉ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ መታወቂያ ካርድ ላይ የዜጎች ጎሳ በዝርዝር የተቀመጠዉ) ዛሬ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊትና የስለላ ድርጅት ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች ሙሉ በሙሉ የተያዙት ወያኔ ዬኔ እያለ በሚጠራቸዉ የትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት ነው፡፡ በፌዴራል የመንግሥት መዋቅርና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ባላቸው እንደ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ የመንገድ ሥራዎች ድርጅት፣ የሲቪል አቪየሽን፣ የኤሌክትሪክና መብራት ኃይል፣ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ባለሥልጣን መ/ቤቶችና ኮርፖሬሽኖች ቁልፍ የኃላፊነት ቦታዎች ባብዛኛው በትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት የተያዙ ናቸዉ።

2. የወያኔ የአኮኖሚ ፖሊሲ የአንድን ብሔረሰብ አባላት ለመጥቀም ሆን ብሎ የተቀየሰ ፖሊሲ ነዉ፡ ለምሳሌ ዛሬ የኢትዮጵያ ዉስጥ እንደ ኮንስትራክሽን፣ ሪል እስቴት፣ ፋይናንስ፣ ትራንስፖርት፣ የውጭ ንግድና የትራንዚት አገልግሎት የመሳሰሉት ዘመናዊ የገንዘብ ምንጭ የሆኑ ዘርፎች በአብዛኛው በትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በሞኖፖል የተያዙ ናቸዉ።

3. የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ያለበት ሁኔታም ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ነጥቦች ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና፣ የሞያና የሕዝባዊ ማህበራት አመራር አባላት በተጠና ሁኔታ ለወያኔ ቅርበት ላላቸው የትግራይ ተወላጆች አሊያም በዘራቸው የትግራይ ተወላጆች በሆኑ ሰዎች እየተያዙ ነው፡፡ ከሁሉቱም ያልሆኑ ኢትዮጵያዊያን የወያኔ ሎሌዎች እስካልሆኑ የመረዳዳ ማኅበር እንኳን ማቋቋምና መምራት እንዳይችሉ ተደርገዋል፡፡

ወያኔ የሚከተለዉ የዘረኝነት ፖሊሲ በኢትዮጵያ አንድነት ላይም ያነጣጠረ አደገኛ ሴራ ነዉ። ተጨቁነናል፤ ተበድለናል፤ ተረግጠናል ብለዉ ጠመንጃ ጭምር አንስተዉ የሚታገሉ ብሔረሰቦች ባሉበት አገር ዉስጥ አንድን አናሳ ብሔረሰብ ለብቻዉ አጉልቶ የሚያወጣ ሌሎችን የሚያቀጭጭና ከፖለቲካዉ ስርአት የሚያገል ዘረኛ ፖሊሲ የአገራችን የኢትዮጵያን አንድነት ወዴት እንደሚወስደዉ መገመት አያዳግትም። የኢትዮጵያ ህገ መንግስት <u>አንቀጽ 8.1</u> የኢትዮጵያ ብሔር፤ ብሔረሰቦች፤ ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉአላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸዉ። <u>አንቀጽ 39.1</u> ማንኛዉም የኢትዮጵያ ብሔር፤ ብሔረሰብ፤ ህዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለዉ መብቱ በማንኛዉም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነዉ። እንግዲህ ልብ በሉ በህገ መንግስቱ መሰረት ኢትዮጵያ የምትባለዉ አገር ዛሬ ከምናዉቃት መልኩ አንሳ ልትገኝ ጫን ያለዉ ከመጣ ደግሞ ጭራሽ ላትኖር ትችላለች ማለት ነዉ፤ ወይም የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት በብሔር ብሔረሰቦቿ ፊርማ ሊቆም ወይም ሊከትም ይችላል። እኛ ኢትዮጵያዉያን በብዙ በተለያዩ ነገሮች ላይ ልንለያይና ላንግባባ እንችላለን ሆኖም ኢትዮጵያ ማናት በሚለዉ ነገር ላይ አንድ አቋም ሊኖረን ይገባል።

ህዝቦች በዲሞክራሲ ስርአት ባልተሳሰሩበትና የህግ የበላይነት በሌለበት በማንኛዉም አገር ኃይለኛዉ ደካማዉን መብደሉ አይቀርም፡በተለይ ኢትዮጵያን በመሳሰሉ ሁለትና ከሁለት በላይ ብሔረሰቦች በአንድ ላይ በሚኖሩበት አገር ጥሬ ኃብትን ለመቆጣጠርና በፖለቲካዉ መስክ የበላይ ለመሆን ሁሌም ቢሆን በተለያዩ ብሔረሰቦች መሀል ትግል ይካሄዳል። ይህ ትግል አድጎ ጦርነት ደረጃ ሲደርስ ተጨቁነናል የሚሉ ብሔር ብሔረሰቦች ጦርነቱን እንደ ሊበሬሺን ጦርነት ይመለከቱታል። የገገር መደቦች ደግሞ ጦርነቱን ስልጣናቸዉንና የኤኮኖሚ ጥቅማቸዉን እንደሚያስጠብቅ ህጋዊ ጦርነት ይመለከቱታል።እንደዚህ አገር ለሁለት ተከፍሎ ሲዋጋ ደግሞ ሰላም፤ መረጋጋትና፤ እድገት ይጠፉና የሰዉ ልጅ እንኳን ለራሱ ለጎረቤቱ ህይወት የሚኖረዉ እሴትና ጣዕም እየደበዘዘ ይሄዳል።

እዚህ ላይ አንድ ልናዉቀዉ የሚገባን ነገር አለ- በብሔር ብሔረሰቦች መካከል ያለዉ አለመግባባት እየሰፋና ስር እየሰደደ በሄደ ቁጥር የህብረተሰቡን አመለካከት የሚበርዝ የጎሳ ርዕዮተ አለም (አይዲዮሎጂ) በየሰዉ አዕምሮ ዉስጥ ይፈጠራል። ይህ ርዕዮተ አለም የብሔር ብሔረሰቦችን ግኑኝነት የተለያየ ፎርምና ይዘት ይሰጠዉና የበዳይና የተበዳይ ጎራ እየለየ መጥቶ ህብረተሰብ በሁለት ይከፈላል። በዚህ ለሁለት በተከፈለ ህብረተሰብ መሀል የሚፈጠረዉ ክፍተት እየሰፋ በሄደ ቁጥር ጨቋኝና ተጨቋኝ ብሔረሰቦች የየራሳቸዉን ርዕዮተ አለም አብራቸዉ እንደ ቆየ የረጂም ግዜ እዉነት አድርገዉ ይቀበሉታል።ለጨቋኝ ብሔረሰቦች ይህ እዉነት የበላይነት፤ጨዋነት፤ ራስን የተሻለ አደርጎ ማቅረብና ትልቅነት ነዉ፤ ለተጨቋኝ ብሔረሰቦች ደግሞ ጥላቻ፤ምሬትና፤ ቂም በቀል ነዉ።እነዚህ ሁለት የተለያዩ እዉነቶች ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ይተላለፋሉ። እነዚህ እዉነቶች ባሉበት አገር ደግሞ በግለሰብ ወይም በቡድን ደረጃ የሚደረጉ ማህበራዊ፤ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግኑኝነቶች ሁሉ የኤትኒክ/የጎሳ አይዲዮሎጂ ይንፀባረቅባቸዋል። እንግዲህ ለሁላችንም ግልፅ እንደሆነዉ የሰዎች አንጎል እንደ ጥቁር ሰሌዳ ለረጂም ግዜ የያዘዉን ነገር በቀላሉ አጥፍተን ሌላ የምንፅፍበት ስላልሆነ የኤትኒክ ችግሮቻችንን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ብንፈታም የጥላቻዉ ርዝራዥ ለረጂም ግዜ ይቆያል ማለት ነዉ። ዝነኛዉ የኤይሪሽ ደራሲ ፈላስፋና ተመራማሪ ኤድመንድ በርክ በአንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር፡ "የክፋት ኃይል የሚያሸንፈዉ መልካምና ደጋግ ሰዎች ክፋት ሲሰራ በዝምታ ስለሚመለከቱ ነዉ" ዛሬ በየቦታዉ እየሄድን የወያኔን ዘረኝነትና ጠባብነት የምንዋጋዉና ለህዝብ የምናሳዉቀዉ ኤድመንድ በርክ ከ200 አመታት በፊት ስላስጠነቀቀን ብቻ አይደለም። ዘረኝነትን መዋጋትና አገራችንን ከጥፋት ማዳን ብሄራዊና ሰብዓዊ ግዴታችን ስለሆነም ጭምር ነዉ።

በአገራችንም ሆነ በሌሎች አገሮች እንደተመለከትነዉ ሰዎች ከነሱ ጎሳ የወጣ መሪ ያሰኘዉን ሲያደርግ እያዩ ምንም አይናገሩም ይህ ቂጥ ያጣ ዝምታ ደግሞ ተመልሶ እነሱኑ ሲጎዳ በተደጋጋሚ ታይቷል።ለምሳሌ ጎረቤት አገር ኬንያ ዉስጥ ጆሞ ኬንያታ የተለያዩ ጎሳ አባላትን ሲያንገላቱና ኪኩዩዎችን ሲጠቅሙ ኪኩዩዎች አንድም ግዜ ኬንያታን አዉግዘዉ አያዉቁም፤ጆሞ ኬንያታ በዳንኤል አራፕ ሞይ ተተክተዉ ኪኩዩዎች ተበደልን ሲሉ ደግሞ ተራዉ የካለንጂኖቹና የማሳዮች ሆነና እኑም በተራቸዉ ዝምታን መረጡ። ይህ የሚያሳየን ትግሬ ሆንን ሲዳማ፤አማራ ሆንን ኦሮሞ፤አኝዋክ ሆንን ሙርሲ ወይም ሶማሌ አንድ መሪ ከዬትም ይምጣ ከዬት በደል ሲፈፅም ካየን በደሉን ፊት ለፊት መኮነን እንደሚገባንና በደልን በምንም አይነት መልኩ ያለመቀበል ባህል ማዳበር እንዳለብን ነዉ።

**ክፍል 3 በሚቀጥለው ሳምንት እናቀርባለን**

## ወያኔ ለውጭ ከበርቴዎች እየሸጠ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ብሎ መገመት የዋህነት ነው።

እናም ምርት ለማፈስ ሲሉ የሚጠቀሟቸው ኬሚካሎችም በሰው ልጆች ጤንነት፣ በአፈራችን፣ በውሃዎቻችንና በከባቢው አየር ደህንነት ላይ የሚኖረው ዘላቂ ጉዳት ካሁኑ መገመት ይሰቀጥጣል። ለሰብሎቻቸው የሚጠቀሟቸው ዘሮችም የአገራችንን ብዘሃ-ህይወት በዘላቂነት ሊያበላሹ ይችላሉ።

በግንቦት7 ንቅናቄ እምነት ይህ ክስተት ወያኔ ጊዜዓዊ ጥቅም እስካገኘ ድረስ ኢትዮጵያን በዘለቄታው የሚጎዳን ነገር በደስታ የሚሠራ ወራዳ ሥርዓት መሆኑን ያመለክታል። ወያኔ የሕዝብ ውክልና የሌለውና በጉልበት እየገዛ ያለ ኃይል ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳ ቡድን መሆኑን በተግባር እያሳየን ነው። ወያኔ ሚኒሊክ ቤተመንግስት ውስጥ እስካለ ድረስ ለም መሬታችንን ለባእዳን መሸጥን የመሰለ የባንዳነት ተግባራትን መፈፀሙ የማይቀር ነው። እናም ግንቦት7 ቀዳሚ ተግባራችን ወያኔን አስወግደን በምትኩ የሕዝብ ውክልና ላለው መንግሥት ምሥረታ ሁኔዎችን ማመቻቸት ነው ብሎ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል።

ስለሆነም የግንቦት7 ንቅናቄ የሚመለከታቸው ሁሉ የሚከተሉትን ነጥቦች በአንክሮ አዳምጠው ተግባራዊ እርምጃ እንዲወስዱ በጥብቅ ያሳስባል።

1. ዛሬ ወያኔ እየፈጸማቸው ያሉት ፀረ-አገርና ፀረ-ሕዝብ ውሎች ነገ የሕዝብ ውክልና ያለው መንግሥት ሥልጣን በሚይዝበት ወቅት የሚፈርሱ መሆናቸው ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ አውቀው ከአሁኑ እጆቻቸውን እንዲሰበስቡ እናስጠነቅቃለን፤
2. የሚመለከታቸው መንግሥታት ሁሉ ዜጎቻቸው በኢትዮጵያ የመሬት ንግድ ውስጥ እንዳይሳተፉ እንዲያሳስቡ እንመከራለን፤
3. በኢትዮጵያ መፃዒ ታሪክ ውስጥ አዎንታዊ ተሳትፎ ያላቸው የፓለቲካም ሆነ የሲቪክ ማኅበራት በዚህ ጉዳይ ላይ የጋራ አቋም ይዘን እንድንቀሳቀስ እንጠይቃለን።

የወያኔ የአገራችንን ለም መሬት ለባእዳን መሸጥ ያንገበገበን ሁሉ ስለ መፍትሄው ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል። እንደ ግንቦት7 እምነት ለዚህ ችግር የማያዳግም መፍትሄ ወያኔን ከሥልጣን ማስወገድ ነው። ሁላችንም የቻልነውን ድንጋይ ከወረወርን የወያኔ እድሜ ብዙዎች ከሚገምቱት እጅግ ያጠረ

## መለስ ባደገኛ የጤና መታወክ ውስጥ . . . ከገጽ 1 የዞረ

የተወሰኑ የወያኔ ባለስልጣኖች ምክክር መጀመራቸውንም ለማወቅ ችለናል። የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የህውሀት አባላት፣ መለስን ሊተካ የሚችል ሰው በማፈላለግ ላይ መሆናቸውን ሲታወቅ፣ በብአዴን በኩልም የእስካሁኑ ይብቃችሁ ከእንግዲህ ቦታውን ለእኛ ልቀቁልን የሚሉ ጥያቄዎች በመምጣት ላይ ናቸው። ይህን የብአዴንን ጥያቄ ማስተናገድ የማይፈልገው ህወሀት፣ ጥያቄ አቅራቢዎችን ለመምታት እቅድ እንዳለውም ለማወቅ ተችሏል።

መለስ ዜናዊ ብራሰልስን የመረጠበት ምክንያት በአውሮጳ ህብረት የወያኔ አምባሳደር ሆኖ በማገልገል ላይ ከሚገኘው ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ጋር ባለው ልዩ ቅርበት ምክንያት እንደሆነ ይታወቃል ያሉት ምንጮቻችን ፣ ሁለቱ ግለሰቦች በራካታ ሀብትና ንብረት በመዝረፍ ስራ ላይ መጠመዳቸውንም አክለው ገልጸዋል ።

## የአንድነት ፓርቲ ስብሰባ በረብሻ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በማናቸውም ጨካኝና ተራ የዱርዬ ስራዎች በመናድ ላይ ያለውን የስልጣን መንበር ማቆየት የሚፈለገው ወያኔ፡ የመንደር ዱርዬዎችን አሰልጥኖ የተቋዋሚ ፓርቲ መሪዎችን እና አባላትን ማንገላታ እና ማስደብደብ ከምርጫ 97 በሓላ እንደትልቅ ስትራቴጂ አድርጎ ይከተለው እንደነበረ አይዘነጋም።

ጫት እና የተለያዩ አደንዛዥ እጾችን እየተጠቀሙ ከወያኔ ደህንነቶች ጋር አብረው የሚሰሩት ድርዮዎች ከፈጸሟቸው ተዘርዝረው ከማያልቁ አጸያፊ እና አስነዋሪ ድርጊቶች መካከል በዶክተር ያእቆብ ሀይለማሪያም ላይ ምራቅ መትፋታቸው፤ዶክተር ብርሀኑ ነጋን ለሰአታት ቅንጅት መግቢያ አካባቢ አግተው አጸያፊ ስድስ መስደባቸው ና የዶ/ር መረራን መኪና መስበራቸው ይጠቀሳሉ።

ወያኔ በመጪው ምርጫ ጎላ ብለው ሊታዩ ይችላሉ ያላቸውን የተቋዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ለማሸማቀቅ፣ በቀድሞ የእርሻ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ በርካታ ድርዬዎችን አስገብቶ ማሰልጠኑን መዘገባችን አይዘነጋም።

## እነ ልደቱና የወጣቶች ማህበር ልዩ የስለላ . . . ከገጽ 1 የዞረ

የግንቦት ሰባት የትግል ስትራቴጂ ተቀባይነት በህዝባችን ውስጥ ከቀን ወደ ቀን እያደገ መምጣት እንደሆነና በወያኔ አጋር ድርጅቶች ውስጥ ሳይቀር ሰርጎ በመግባት እያስከተለ ያለው ትርምስና ውዥንብር በአጭሩ ካልተገታ በዋንኛነት ተጎጂ የሚሆነው ህወሀት "የልማትና የእድገት ተጠቃሚ ሆናችኋል የሚላቸው " ካድሬዎች ፤ የደህንነትና የመረጃ ሰራተኞች፤ ፖሊስና የመከላኪያ ሰራዊት እንደሚሆን ማስፈራሪያ አዘል መልዕክት እንደነበረ ተያይዞ የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

ወያኔ አክራሪ ናቸው ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች ተከታዮች ለማደን ይረዳኛል ከሚል ፍጹም ቀቢጸ ተስፋ በልደቱ አያሌው የሚመራውን ኤዴፓ ለመጠቀም እንደወሰነ በስብሰባው ላይ የተነገረ ሲሆን፣ በቅርቡም በጸጥታ ጉዳዮች ከኢዲአፓ ጋር ለመስራት ስምምነት ተደርሷል ተብሎ በመገናኛ ብዙሀን የተገለጸው በዚሁ ምክንያት እንደሆነ ታውቋል።በተለይም በግንቦት ሰባት እና አንድነት ፓርቲ መካከል አለ ተብሎ የሚጠረጠረውን ሚስጥራዊ ግንኙነት ማነፍነፍ እና ለወያኔ ማቀበል እንዲችል ሀላፊነቱ ለኢዴፓ እንደተሰጠውም ታውቋል።

ወያኔ ለስርዓቱ ታማኝ ናቸው በማለት በወጣቶች ፎረም ካሰባሰባቸው ግለሰቦች አንዱ የነበረው ኤርሚያስ ለገሰ፣ በሚንስትር ዴታ ማዕረግ የበረከት ስምኦን ምክትል ተደርጎ በኮሚንኬሽን መ/ቤት በተመደበ በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ አገርንና ህዝብን ለውድመት በመዳረግ ለመሞት ከቆመ የወንጀለኞች ቡድን ጋር እስከ መጨረሻው ላለ መቆም በወሰደው እርምጃ፣ ለሥራ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንደተላከ በዚያው በመቅረቱ ከርሱ ጋር ቅርበት የነበራቸው የወያኔ ጀሌዎች በሙሉ በአይነ ቁራኛ እንዲጠበቁ ምስጢራዊ ትዕዛዝ መሰጠቱም በዕለቱ እንደተገለጸ ታውቆአል።

ባለፈው ቅዳሜ በተካሄደው በዚህ ሚስጥራዊ ስብሰባ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያነጋገረ ያለው በቤተክርስቲያንቱ ውስጥ የተፈጠረው ቀውስ የፖለቲካ ዓላማ እንዳለው ተቆጥሮ ከፍተኛ ክትትል እንዲደረግና እርምጃ እንዲወሰድ ትዕዛዝ መሰጠቱም ተገልጾአል። በውይይቱ ወቅት በምሳሌነት የተነሳው በቃሊቲ አካባቢ የሚገኙ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ጉዳይ ሲሆን ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው ሰዎች በአካባቢው እየተንቀሳቀሱ ስለሆነ ልዩ ክትትል መደረግ አለበት መባሉን የስብሰባውን ሂደት በቅርበት የተካታተሉት የውስጥ ምንጮች ለዘጋቢያችን አስታውቀዋል።

ወያኔ በጸጥታ ስጋት ሽፋን በተቃዋሚነት የሚፈርጃቸውን ለማጥቃት ስልት የቀየሰ መሆኑ ተደጋግሞ የተገለጸ ነው ያለው ዘጋቢያችን፣ የጥቂት ዘረኞች አፈና ያንገፈገፈው ህዝባችን ወያኔን ለማስወገድ ለሚደረገው የሞት ሽረት ትግል በቂ አመራር የሚሰጠውን የፖለቲካ ሃይል ብቻ እየተጠባበቀ እንደሆነ ከላከልን ዘገባ ጋር አያይዞ ገልጾአል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ በተባበረ ህዝባዊ ትግል ለማፍረስ እንዲቻል ህዝቡ የሚጠብቀውን ጠንካራ አመራር ለመስጠት የሚችል ሃይል ለመፍጠር ከሁሉም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የጀመረው ድርድር በቅርቡ ፍሬ ያፈራል ብሎ እንደሚጠብቅ ገልጿል።

## የኦሮሞ ግንባርን እንቅስቃሴ የሚያሳይ . . . ከገጽ 1 የዞረ

የኬኒያው ኔሽን ሚዲያ ቴሌቪዥን የኦነግ ታጣቂዎች ሲሰለጥኑና ለውጊያ ሲዘጋጁ የሚያሳይ ምስል ቀርጾ ያቀረበ ሲሆን ይህም በአገሪችን አራቱም ማዕዘናት የወያኔን አፈና ለማስወገድ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች መኖራቸውን ገሃድ በማውጣት የወያኔ መሪዎች በሚቆጣጠሩት ሚዲያ አንድም ለጸጥታ የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ ለማስመሰል ይልቁንም የልማት መንግሥት ነኝ ባዩ አገዛዝ ሰላም የኢኮኖሚ እድገት አምጥቻለሁ የሚለውን የውሸት ፕሮፖጋንዳውን ባዶ እንዳስቀረበት ታውቆአል:: የኔሽን ቲቪ ጋዜጠኞች በኦነግ ታጋዮች ሽፋን ሰጭነት የኢትዮ-ኬኒያ ድንበርን አልፈው በኦነግ ይዞታ ስር ባለው ቦታ ለሶስት ቀናት መቆየታቸው አስታውቀዋል። በርካታ የኦነግ ተዋጊዎችን የቀረጹት የኔሽን ቲቪ ጋዜጠኞች ምልምል የኦነግ ሰልጣኞች የሚሰጣቸውን ከባድ ወታደራዊ ስልጠና በአይናችን ተመልክተናል ብለዋል።የቴሌቭዥን ፕሮግራሙ ለኦነግ በሰጠው ሰፊ ሽፋን የተደናገጠው ወያኔ አምባሳደር ብሎ ባስመቀመጠው አሻንጉሊቱ ዲሳሳ ድሪቢሳ «ኦነግ ሽብርተኛ ብድን ነው፤ እንቅስቃሴውን ጸረ ዴሞክራሲያዊ እና ጸረ ሰላም ነው» ማለቱ ታውቋል።

ኔሽን ሚዲያ ግሩፕ በተደጋጋሚ የሲኤን ኤን ያመቱ ምርጥ የሚዲያ ተቋም አሸናፊ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን በአፍሪካ አሉ ከሚባሉ የመገናኛ ብዙሃን ውስጥ በግንባር ቀደምነት የሚጠቀስ ነው።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org